በኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ የስነጽሑፍ ክፍል የተዘጋጀ

# አሸባሪ መንግሥት መውደቂያው ሲቃረብ ተቃዋሚውን ሁሉ አሸባሪ ይላል!

ሚያዝያ 29 ቀን 2015 ዓም(07-05-2023)

ሽብር ማለት የሰውንም ሆነ የእንስሳትን እንዲሁም የከባቢን እረፍትና ሰላም መንሳት፣ ማስጨነቅ፣ማዋከብ፣መግደል ፣ማፈናቀል፣ማፍረስ፣ መናድና ማውደም ማለት ነው።በነዚህ ተግባራት የተሰማራ ሁሉ ሽብርተኛ ወይም አሸባሪ ይባላል። ሽብር በግለሰብና በቡድን እንዲሁም ፣መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ አካላት ሊፈጸም ይችላል።ለዘረፋ ሲባል በሽፍታና በወንበዴ የሚፈጸመው ሽብር ለዋሪውን ማህበረሰብ ስጋት እንደሚሆንበትና እንደሚያሸብረው ሁሉ በመንግሥትና በተቋማቱ የሚፈጸመው ደግሞ አገርና ሕዝብን የሚጎዳ፣ሰላምን የሚያደፈርስና ጦርነትን የሚጋብዝ፣አገር አፍራሽ ሕዝብ አጫራሽ ሽብር ይሆናል። በሌላ መልኩ አሸባሪን ሃይል ከሚፈጽመው የሽብር ተግባራት ለማገድ ወይም ለማስቆም ሲባል የሚደረግ ትግልና የሚወሰድ እርምጃ በአሸባሪው ዘንድ ጭንቅና ብርክ የሚለቅ፣የሚያስፈራና የሚያሸብር ይሆናል።ለዚያም ነው አሸባሪ መንግሥት ተቃዋሚውን ሁሉ አሸባሪ በማለት የሚፈርጀው።በመንግሥት እይታ ትክክል ነው።ከያዘው ሥልጣን የሚያወርድ፣በሰራው ወንጀል የሚጠይቅ ሕዝባዊ ሃይል ሲነሳበት እንዴት ሽብር አይለቅበት?እንዴት አሸባሪ ተነሳብኝ አይል? ሽብር ሁለት አይነት ሕዝባዊና መንግሥታዊ የሆነ ገጽታ እንዳለው በዚህ እንረዳለን።

ከዚህ እይታ ስንነሳ ለአገር አንድነት ፣ለሕዝብ እኩልነት፣ለፍትሕና ለዴሞክራሲ የሚታገል፣ጸረ ጎሰኝነት አቋም ያለው ሁሉ በአሸባሪው መንግሥት ዓይን አሸባሪ ከተባለ እኛም አሸባሪዎች ነን፤እንኮራበታለን እንጂ አናፍርበትም።የሚያሳፍረው ሕዝብን ከሚያሸብር ጎሰኛ መንግሥት ጋር አብሮ መሰለፍ ነው እንጂ ከሚሸበር ሕዝብ ጋር መቆም አይደለም።ሽብርን በሽብር መመለስ የተፈጥሮ ግዴታ ነው።ጦርነት በተፈጥሮው አውዳሚ ነው።የሰው ልጅም ሰላምን እንጂ ጦርነትን አይሻም። ሆኖም ግን በተለያዩ ምክንያቶች በአረመኔዎች ሲገደል፣ሲጨፈጨፍ የመጨረሻ ምርጫው ፣ህይወቱን ለማዳንና መብቱን ለማስከበር ሲል ለጦርነት መሰለፍ ነው።ጠላትን በመጣበት መንገድ ለመመለስ ይገደዳል። በግልጽና በስውር ጦርነት ይሳተፋል።የሽምቅ ውጊያ አንዱ ስልቱ ሲሆን ጠላት ሳያስበውና ሳይጠብቀው ዱብ ዕዳ ወይም ቅጽበታዊ የሽብር ዱላ ማሳረፍ ነው።በዚያን ጊዜ የጠላት ሰፈር ይረበሻል፣ይሸበራል፣ይበታተናል።

ሌላው የጨካኝ መንግሥታት የሽብር ዘመቻ በፕሮፓጋንዳው መስክ የሚነዛው ዘመቻ ነው።የጠላትን ስነልቦና ለማለዘብና ሞራልን ለመስበር፣እርኩስ አድርጎ በመሳል ተከታይ እንዳይኖረው ለማድረግ ሲባል በበሬ ወለደ ትርክት የታጨቀ የነጭ ወሬ ጋጋታ ማራገቡ

አንዱ ስልት ነው።ከዚያም አልፎ ተርፎ የሚዘገንን ግድያና ወንጀል ፈጽሞ በተቃዋሚው ላይ መደፍደፍ ሌላው የአሸባሪዎች የፕሮፓጋንዳ ሥራ ነው። በሕዝብ ድጋፍ የሌላቸው አምባገነኖች ይህንን እንደ ዋና መሳሪያ ይጠቀሙበታል።በታሪክ መለስ ብለን አንዳንዶቹን ብናነሳ የቺሊው አምባገነን ጄነራል አውጉስቶ ጆሴ ራሞን ፒኖቼ በተቃዋሚው ላይ የፈጸመውን የማጥቃት እርምጃ እንዴት እንዳስኬደው ብናይ በሌሎቹና አሁንም በእኛ አገር አምባገነኑ አብይ አህመድ በተመሳሳይ መልኩ እንደተጠቀመበት በሰሞኑ የራሱ ተላላኪ ላይ የፈጸመው ግድያ ትልቅ ማስረጃ ነው።

ፒኖቼ በሕዝብ የተመረጠውን የሶሻሊስት ፓርቲ መሪ ሳልቫዶር አሌንዴን በአሜሪካኖቹ ትዕዛዝና ድጋፍ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በሴፕቴምበር 11 ቀን 1973 ዓም በኩዴታ ገሎ በማሶገድ ቤተመንግሥቱን በመቆጣጠሩ የሕዝቡ ተቃውሞ ሲነሳበት የሽብር ዘመቻውን ከፈተ።ከቃላት አልፎም በዬቦታው ፈንጂ እያስቀበረ የብዙ ዜጎችን ህይወት ቀጠፈ።ድርጊቱን በተቃዋሚዎቹ ላይ በመደፍደፍ በተለይም በሶሻሊስቶቹና በደጋፊዎቻቸው ላይ የክተት አዋጅ አውጆ ለብዙ ሽህ ዜጎች ሞት ምክንያት ሆነ።በዚህ የሽብር ድርጊቱ ለዓመታት በሥልጣን ላይ ለመቆዬት ቻለ።የሕዝቡን ትግል ግን ሊያስቆመው አልቻለም።በመጨረሻም ከስልጣን ወርዶ ከአገር ወጣ። እንደ ፈረስ ሲጋልቡት የኖሩት አሜሪካኖችና ምዕራባውያን ከመውደቅ ሊያድኑት አልቻሉም። በአውሮፓ በተለይም በእንግሊዝ አገር ተሸሽጎ ሲኖር በዓለም አቀፉ ፍርድ ቤት የመቅረብ አደጋው ሲጋረጥበት በእንግሊዝና በአሜሪካኖቹ ተከላካይነት በበሽታ ምክንያት እራሱን ሊከላከል አይችልም በሚል ሰበብ ከፍትሕ ተደብቆ ሲኖር አገሩ ከገባ በኋላ ጥቂት ቆይቶ በማያመልጠው የተፈጥሮ ሞት ይህችን ዓለም በ91 ዓመት ዕድሜው በዲሴምበር 10 ቀን 2006 ዓም ተሰናበተ።ፒኖቼ የከፉ መሪዎች ምልክት ሆኖ ቀረ።ሌላው የአርጀንቲና አምባገነኑ ዮርግ ራፋኤል ፊዴላም እንዲሁ በአሜሪካኖች ትእዛዝ ኩዴታ ፈጽሞ ሥልጣን ከጨበጠ በኋላ የብዙ ዜጎች በተለይም የሶሻሊስቶች ህይወት እንዲቀጭ አደረገ። በአውሮፕላን ሳይቀር እዬጫነ ወደ ባሕር እስከመወርወር የደረሰ ጭካኔ ፈጸመ። ይህ አምባገነን ግን ከፍትሕ ሊያመልጥ አልቻለም፤የሕዝቡ ትግል ጊዜውን ጠብቆ በአገሪቱ ለውጥ ሲመጣ በፈጸመው ወንጀል ተጠያቂ ሆኖ ሲያጉርና ሲያሰቃይ በነበረበት የእስር ቤት ጉረኖ ለዕድሜ ልክ ተፈርዶበት ተወረወረ።በእስር ቤት እንዳለ በታሰረ በሶስተኛው ዓመት በሜይ 17 ቀን 2013 የዛሬ 10 ዓመት በተወለደ በ87 ዓመቱ ታሞ ሞተ።እነዚህ አምባገነኖች ጥለውት የሄዱት መታሰቢያ ቢኖር ለቤተሰቦቻቸው ሳይቀር ሃፍረትን ነው። ከነዚህ ያልተማሩ የዘመናችን አምባገነኖችም የፈጸሙትና አሁንም በመፈጸም ላይ ያሉት ኢሰብአዊ ወንጀል ቢበልጥ እንጂ አያንስም።በነዚህ መነጽር በአፍሪካ መሬት ላይ የበቀሉትን ጥቂት አምባገነኖች ስናይ የሚከተሉትን እናገኛለን።

ከላይ ወደታች ስንወርድ የቱኒዝያው አምባገነን ቤን አሊ ተቃዋሚውን ሁሉ አሸባሪ እያለ ሲፈጅ፣ሲያስርና ሲያሰቃይ ኖሮ በ2011 ዓም በተቀሰቀሰው ሕዝባዊ ተቃውሞ ከሥልጣን ተወግዶ በስደት በሳውዲ አረቢያ ለስምንት ዓመት ያህል ኖሮ በ2019 ሞተ።በቱኒዝያ

የተቀሰቀሰው ሕዝባዊ ተቃውሞ ምህዳሩን አስፍቶ ሊቢያንና ግብጽንም አመሳት።ከሰላሳ ዓመት በላይ በሥልጣን ላይ ተቀምጠው ያሻቸውን ሲያደርጉ የነበሩት አምባገነኖች ፣ ሞአመር ጋዳፊና የግብጹ ሑስኒ ሞባረክ የለውጥ ሰደዱን ሊያመልጡ አልቻሉም።ጋዳፊ በአሰቃቂ መልክ ሲገደል ሑስኒ ሙባረክ ያሻውን ሲያስፈርድ በነበረበት ፍርድ ቤት ችሎት በእስረኛ ወንበር ላይ ሊቀመጥ ቢችልም ስልጣኑን የተረከበው የሱው ታዛዥ የነበረው አልሲሲ በነጻ እንዲለቀቅ ቢያደርገውም ቅስሙ ተሰብሮ ትንሽ ከቆዩ በኋላ በ91 ዓመቱ ሞት ወሰደው።ከዓመታት በፊትም የኛው ጎረቤት አገር የሆነችውን ሱዳንን በኩዴታ ከ30 ዓመት በላይ የፍጥኝ አስሮ ሲገዛ የነበረው ጀነራል አልበሽር በሕዝቡ ትግል ግፊት የራሱ ጀነራሎች እንዲነሱበት አድርጎ ከሥልጣን ተወግዶ የዓለም ፍርድ ቤት ማዘዣ በመጠበቅ ላይ እንዳለ ሥልጣኑን የተረከቡት ጀነራሎች በፈጸሙት ክህደትና የሥልጣን ሽኩቻ በቀሰቀሱት ጦርነት ከእስርቤት አምልጦ እስከአሁን ድረስ ዬት እንዳለ አልታወቀም።ከላይ እንዳዬነው የአምባገነኖች ሁሉ መጨረሻቸው እንደማያምር ተገንዝበናል።በጣም የሚያሳዝነው ነገር የሕዝቡ ትግል በሌሎች አምባገነኖች እዬተጠለፈ የታሰበው ስር ነቀል ለውጥ አለመምጣቱ ነው። ለዚያም ዋና ምክንያቱ የጠራ አቋም ያለው የሕዝቡን ትግል የሚመራ ሕዝባዊ አካል አለመኖሩና ከፍተት በመፈጠሩ ነው።

ወደ ፈረደባት አገራችን ስንመለስ ላለፉት ሃምሳ ዓመታት እስከ አሁን ድረስ በጨካኝና ከሃዲ አምባገነኖች መዳፍ ስር ወድቃ እንደላሸቀችና ሕዝቧም መከራና ፍዳ ሲቀበል እንደኖረ አይካድም። የትኞቹም ቢሆኑ በፈጸሙት ወንጀል ሳይጠየቁ የሞቱና በስደት ላይ ያሉ አሁንም በሥልጣን ኮርቻ ላይ የተቀመጡት የዚያው አሸባሪ ስርዓት ባለቤቶች መሆናቸው የሚታወቅ ሃቅ ነው።ስማቸው ቢለያይም ጸረ አገርና ጸረ ሕዝብነታቸው በአንድ እረድፍ ያሰልፋቸዋል።

ለ17 ዓመት ስልጣኑን በጉልበት የተቆጣጠረው የደርግ ወታደራዊ አምባገነን ስብስብ ሕዝብን በማሸበር፣ወጣቱንና የተማሩትን፣ለአገር ብዙ ውለታ የሰሩትን በመግደል ብዙ ወንጀሎች ከፈጸመ በኋላ በሕዝቡ ትግል ተወገደ፣መሪዎቹም የተያዙት ተይዘው ያልተያዙት ከመሪው ከአረመኔው መንግሥቱ ሃይለማርያም ጭምር በአሜሪካኖቹ እርዳታ አገር ጥለው ፈረጠጡ።እስከአሁንም ድረስ ለፍርድ ሳይቀርቡ በያገሩ ተበትነው ድምጻቸውን አጥፍተው ይኖራሉ።መንግሥቱ ሃይለማርያም ሊቢያን በጎበኘበት ጊዜ ከጋዳፊ ለኢትዮጵያ የተሰጠውን 150ሚሊዮን ዶላር እርዳታ ከአገሪቱ ካዝና ዘርፎ ከመሰሎቹ ጋር ተቀራምቶ በዚምባብዌ የንግድ ዘርፍ ላይ በማዋል ከገሪቱ ሃብታሞች እረድፍ ተሰልፏል።ቀደም ሲል አጎቱን አስራት ወልዴን በዝምባብዌ የኢትዮጵያ አምባሳደር አድርጎ በመሾም ሁኔታዎቹን እንዲያደላድልለት ማለትም የእርሻ መሬትና መኖሪያ ቤቱን እንዲያዘጋጅለት ማድረጉ ያደባባይ ሚስጥር ነው።ሆኖም ግን የኋላ ኋላ ሌቦች ሲሰርቁ ይስማማሉ፣ሲካፈሉ ይጣላሉ እንደሚባለው በተሰረቀው ገንዘብ ድርሻ ላይ ጠብ ተነስቶ በጥቅም ተጣልተው ከቆዩ በኋላ አጎቱ በሞት ይህችን ዓለም ተሰናብቷል። መንግሥቱ ሃይለማርያምን እንደ አገር ወዳድ የሚቆጥሩት ጥቂት አይደሉም፤አገር

መውደድ ማለት ምን እንደሆነ መረዳት ያቃታቸው ወይም የወንጀሉ ተባባሪ የሆኑት ብቻ ናቸው።አገር ማለት ሕዝብ ነው።ድንጋይና አፈሩ አይደለም፤ያገራችን ዘፋኝ እንዲህ ሲል አንጎራጉሯል

ከጎራው ወጥቼ እስኪ ልነጋገር፣

አለሰው ቢወዱት ምን ያደርጋል አገር?

ሰው ሰው ካልሸተተ ድንጋይና አፈር፣

ባዶ መሬት እንጂ አይባልም አገር።

ሌላው አገሩን ቀርቶ ቤተሰቡንም የማይወድ ጭራቅ መሆኑን ደግሞ የሚያሳዬው ደርግን ከተቀላቀለ በኋላ የሊቀመንበርነቱን ቦታ መያዙን የሰማው ሃረር የሚገኘው ሶስተኛ ክፍለጦር ወደ ክፍሉ እንዲመለስ ጥሪ ሲያደርግለት እምቢ በማለቱ ቤተሰብህ ላይ፣ (በሚስትና ልጆችህ ላይ) እርምጃ እንወስዳለን ሲሉት ስትፈልጉ ቀቅላችሁ ብሏቸው ያለው አባባሉ ከሥልጣኑ በላይ ለቤተሰቡም ቢሆን ፍቅር እንደሌለው የሚያሳይ ነው።ይህንን ጨካኝ ሰው ነው አገር ወዳድ እያሉ የሚያሞካሹት!የደግ ሰው ማንነቱ የሚለካው በቅርቡ ባሉት ላይ የሚያሳዬው እሩህሩህነትና ሃላፊነት ነው። ለጤነኛ ሰው ከልጅና ከሚስት፣ ከናትና ከአባት፣ከእህትና ከወንድም እንዲሁም ከአገር በላይ የሚወደድ የለም።እነዚህን ሁሉ ቀብድ አሲዞ ነው በሥልጣኑ ላይ ሙጭጭ ማለቱን የመረጠው።የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ለቤተሰብ አዛኝና እሩህሩህ በመሆኑ የሃረር ጦርም ያሰበውን እርምጃ ሳይወስድ ለውጥ ያንሳው ብሎ ተወው።

ሰው የሆነ ሰው እንኳንስ በቤተሰቡ ላይ ቀርቶ ባሳደገው ውሻም ላይ ቢሆን ክፉ ነገር እንዲደርስበት አይወድም፣የሚፈለገውን መስዋእትነት ከፍሎ ያድናል።መንግሥቱ ሃ/ማርያም ግን የማይገባውን ቦታ አለቅም ብሎ በቤተሰቡ ላይ ፈረደ፤አሳልፎ ሰጣቸው። ለ17 ዓመት ያሻውን ሲያደርግ ኖሮ የሕዝቡ ና የተገንጣዮች ትግል ሲጠናከር በፈጸመው ወንጀልና የአገር ክህደት ሳይጠዬቅ፣የፊዴላ፣ የኢዲዓሚን፣የሙባረክ፣ የአልበሽርና ፣የጋዳፊ እጣ ሳይደርሰው ፤አሜሪካኖች ጋር ተመሳጥሮ አገራችንን ለተገንጣይ ሃይሎች አስረክቦ ፈረጠጠ።ለራሴ የምትሆን አንድ ጥይት እስክትቀረኝ ድረስ እጋደላለሁ ያለው ቀዳዳ ወያኔና ሻእቢያ ገና ከተከዜ ሳያልፉ እግሬ አውጭኝ ብሎ ዚምባብዌ ገባ።ጠያቂና ተቆርቋሪ ጠፍቶ ፣የንጹሃን ደም እዬጮኸ መልስ ሳያገኝ እንደ ነጻ ሰው ቴኒሱን እዬተጫወተ ተዝናንቶ ይኖራል።ይህ ሰው በብዙ ዜጋ ህይወት መጥፋት፣በአገር ሃብት ምዝበራና ስርቆት፣ወታደሩን ጦር ሜዳ ላይ አጋፍጦና ማግዶ በመሸሽና በአገር ክህደት መጠዬቅ ያለበት እጥፍ ወንጀለኛ ነው።የናዚ ወንጀለኞች ታድነው በሙቶ ዓመት ዕድሜያቸው ለፍርድ ሲቀርቡ ይህ ወንጀለኛ ከፍትሕ አምልጦ ሊቀር አይገባም።ተባባሪዎቹም እንዲሁ። የወንጀል እሮጌ የለውምና።

የደርጎች በተለይም የመንግሥቱና ተከታዮቹ ለፍርድ አለመቅረብ በአሜሪካኖች ጥላ ሥር የተከናወነ በመሆኑ ለ27 ዓመት ወንጀል ተጠያቂ የሆነው የወያኔ አገዛዝ መሪዎችም የአሜሪካኖች ውጤት በመሆናቸው ያለመከሰስ መብት እንዳላቸው ይሰማቸዋል። የሞራል ድጋፍ ሆኗቸዋል።ማን እንደተጠዬቀ ይጠዬቃል? በሥልጣን በነበሩበት እረጅም ጊዜ ተነግሮ የማያልቅ ግፍና በደል እንዲሁም ዘረፋ ፈጽመዋል። በሕዝቡ ትግል ከሥልጣን ሲወገዱ ክፍተቱን የሞላው አድፍጦ ሲጠብቅ የነበረው የራሳቸው ታዛዥና የወንጀሉ ተባባሪ የሆነው የአሜሪካኖች ጥፍጥፍ ሥራ የሆነው ኦሕዴድ የተባለው የኦሮሞ ቡድን ነው።በሥልጣንና ጥቅም ምክንያት ተጣልተው ሲዋጉ ሕዝቡን ጎራ ለይቶ እንዲዋጋ አድርገውታል። ከሞት የተረፉት የህወሃት መሪዎች የዘረፉትን የአገር ሃብት ይዘው በአፍሪካ፣በአውሮፓና በአሜሪካ የተሞላቀቀ ህይወታቸውን በመምራት ላይ ናቸው። በቀሰቀሱት ጦርነት ከሚሊዮን በላይ ሕዝብ ካስጨረሱ በኋላ በአሜሪካኖችና በአውሮፓውያኑ ጣልቃ ገብነት የእርቅ ስምምነት ፈጽመው ውሾን ያነሳ ውሾ ይሁን ብለው ለዳግም ዘረፋ፣ለዳግም ውድመት፣ለዳግም አገር ብተና ግንባር ፈጥረው በመንቀሳቀስ ላይ ናቸው። ይህም ብቻ አይደለም ብልጽግና የሚል ጭንብል ያጠለቀው ቤተመንግሥቱን የተቆጣጠረው የኦነግ ስብስብ በጫካ ካሰማራው በአማራው ተወላጅና ዓላማውን በማይቀበሉት የኦሮሞ ተወላጆች ላይ ሳይቀር ግድያና ግፍ ሲፈጽም ከቆዬው አሸባሪ ከንፉ ጋር የተለያዬ ዓላማ እንዳለው በማስመሰል ለማወናበድ የተበታተነውን ሃይሉን አሰባስቦ ለማሰለፍ ሲል እርቅ በሚል ሽፋን በታንዛንያ ስብሰባውን ለማካሄድ ወስኖ ውጤቱን በመጠባበቅ ላይ ነው። ይህንን ደባ በሚቃወመው ሕዝብ ላይ በተለይም ለዓላማቸው እንቅፋት የሚሆነውን የጋራ ጠላታችን ነው ብለው በመደቡት የአማራው ተወላጅ ላይ የሽብር አዋጅ ከተት ብለውበታል።ያንንም ለማስፈጸም ሲሉ የጥፋት ድርጊቶችን፣ግድያዎችን እዬፈጸሙ ማላከኩን ስልታቸው አድርገውታል።የሰሞኑ በራሳቸው ተላላኪ በሆነው፣ግርማ የሽጥላ በተባለው የባእዴን አባል ላይ የፈጸሙት ግድያ የዚያ አንዱ አካል ነው። በስበብ የአማራውን ተወላጅ ወንጅሎ ለማጥቃት አብይ አህመድ ከሁሉም በፊት ቀድሞ የሟች ነፍስ መውጣቱ ሳይረጋገጥናገና በጣር ላይ እያለ፣ የሕክምናም ሆነ የፖሊስ ሃይል በቦታው ሳይደርስ ከማንም በፊት ተሽቀዳድሞ ሙሾ ማውረዱና በአማራው ላይ ጣቱን መቀሰሩ የሴራውን መነሻ ፍንትው አድርጎ ያሳያል። በጣት ጥቆማው ብቻም አልተገደበም ይህንን ተገን አድርጎ በተቃዋሚው ላይ የጥፋት ሃይሉን አሰማርቷል።አያ ጅቦ ሳታመሃኝ ብላኝ!ማለት ይህ ነው።

አብይ አህመድ የሚመራው የኦሮሙማው ስብስብ ብርክና ጨንቅ ሲይዘውና ሲሸበር ሕዝቡን ማሸበሩ የተለመደ ተግባሩ ነው።የጦስ ዶሮ እዬፈለገ ይወነጅላል።ከዛሬሁለት ዓመት በፊት በተቃውሞ ሲናጥ፣ ብርክ ሲይዘውና ፣ሽብር ሲለቅበት አሜሪካና አውሮፓ የሚኖሩ ከ15 ያላነሱ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ስድስተኛውን አገራዊ ምርጫ ለማደናቀፍ፣ለአማራው መብትና በአዲስ አበባ ላይ ዝም አንልም በሚል በህቡእ ተደራጅተው ሲንቀሳቀሱ፣የአገር መከላከያ ሚኒስትር፣ብሔራዊ ደህንነትና መረጃ አገልግሎት፣የፖሊስ ኮሚሽንና የኢንፎርሜሽን መረብና ደህንነት ኤጀንሲ ግብረሃይል

ደርሰባቸው ዓላማቸውን አክሽፎታል ሲል በሚያዝያ 27 ቀን 2013 ዓም ባስተላለፈው የራዲዮና ቴሌቪዥን ተደጋጋሚ ሰበር ዜና የግለሰቦቹን ምስል በመለጠፍ ያዙኝ ልቀቁኝ ሲል ቀላምዶ ነበር። የሚገርመው ነገር ሊገለብጠኝ በአገርቤት ሚሽን የተሰጠው አንድ ሰባራ ሽጉጥና የዛገ ሰንጢ የያዘ የቀድሞ ወታደር የነበረ ነው ማለቱም የፍርሃትና የውሸት ደረጃውን ያጋለጠ አስቂኝም አሳፋሪም ትርክት ነበር።የተከሰሱት ኢትዮጵያውያን አብዛኞቹ የማይተዋወቁ መሆናቸው ሲታወቅ የስርዓቱን ከንቱነት ይበልጥ አጋልጦታል።እንደ ቀላል ነገር ማለትም በአገር ቤት እንደሚኖረው ዜጋ እንደፈለገ ሰብስቦ ያሻውን ሊያደርግ እንደማይችል እዬታወቀም ከገቡበት ገብቼ ለፍርድ አቀርባቸዋለሁ በማለት ፎክሮ ነበር። ግን እንኳንስ ከውጭ አገር ለፍርድ ሊያቀርባቸው ይቅርና አንዳንዶቹ አገር ቤት ሲገቡም ሊነካቸው አልደፈረም።

አሁንም የሕዝቡ ትግል እያደገና እዬጠነከረ ሲመጣበት የተለመደ ውንጀላውን በመድገም በውጭና በአገር ውስጥ በሚኖሩ ተቃዋሚዎቹ ላይ የአሸባሪ ሰሌዳ ለጥፎ ያዙኝ ልቀቁኝ እያለ ነው።በአገርቤት ያሉትን ጋዜጠኞችና ለስርዓቱ የማይመቹ ታጋዮች፣የማህበረሰብ አንቂዎች፣መምህራን ---ወዘተ በማንነታቸው እያሳደደ በእስር ቤት ማጎሩን ተያይዞታል። በተለይም በአማራው ተወላጆች ላይ የከተት ዘመቻ አውጆ በኦነግ ተገንጣይ ጦር የተጥለቀለቀውን የመከላከያ ሃይል በአማራው ላይ አዝምቶ ንጹሃንን በመጨፍጨፍ ላይ ነው።የአማራው ተወላጅ ፋኖና ልዩ ሃይልም እምቢ ለአገሬ፣እምቢ ለእኩልነቴ፣እምቢ ለፍትሕ ብሎ መሳሪያውን አንግቦ እዬተፋለመ ነው።

የአማራው እምነትና ማንነት ኢትዮጵያዊነት ነው።ለኢትዮጵያ ሲል ህይወቱን አሳልፎ ይሰጣል።ዘርና ጎሳ፣እምነት አያግደውም።ያንንም በታሪኩ ተጋብቶና ተዋልዶ በሰላም እዬኖረ አሳይቷል።ለእኔ ብቻ የሚል የስግብግብነት ስሜት የለውም።አገሩን ይወዳል። ወገኑንም እንዲሁ።እንኳንስ ለሰው ለእንስሳና ለእጽዋትም የሚራራ  የሞራል ልእልና ባለቤት የሆነ ፍጡር ነው። በደልና ግፍን ይጠዬፋል፣እንኳንስ በራሱ ላይ በሌሎችም ላይ ሲደርስ ዝም አይልም።ለዚያም ነው አገር ወራሪዎች ሞክረው ሳይሳካላቸው ቢቀር አማራውን እንደ ዋና ጠላት ቆጥረው ጠላት የሚያበዙበት፣የሚቀሰቅሱበት።

የአገር ወዳዱ አማራ ዓላማ ከሁሉም ጎሳ ጋር ተጋብቶና ተዋልዶ የኖረባትን ፣ከአያት ቅድመአያቶቹ የተረከባትን አገር ከአምባገነኖችና ፣ከዘረኞች፣ከኋላቀር ዘራፊና ጨካኝ ባንዳዎች አገዛዝ ለማላቀቅ፣እኩልነትን፣ፍትሕን፣አንድነትንና፣ዴሞክራሲን የሚያረጋግጥ የጋራ ስርዓት ለማስፈን ነው።በጎሳ ህሳቤ ተበክለው ኢትዮጵያን ለማፈራረስ የባዕዳንን አጀንዳ ለማስፈጸም እንደተነሱት የህወሃትና ኦነግ ስብስቦች  አይነት አይደለም።የሁሉም ጎሳ ተወላጅ በጋራ የሚመሯትን አገር ለማረጋገጥ እንጂ የአንድ ጎሳ የበላይነትን ለማስፈን አይደለም።

እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ የኦነጉ ተረኛ አገዛዝ ዓላማውን በማጣመም ያለፈ ስርዓት ለማስፈን፣ ሌላውን ጎሳ ለማንበርከክ የተነሳ ነው በማለት የራሳቸውን ጥፋትና ዓላማ በአማራው ላይ

ለጥፈውበታል።እራሳቸውን የእኩልነት ጠበቃ በማድረግ እኩልነትህን የሚንድ፣ ያገኘኸውን መብት የሚቀማ፣ አገር የሚያፈርስ ሊመጣብህ ነውና አብረኸኝ ቁም፣ከጎኔ ተሰለፍ፣ሥልጣኔን ጠብቅ፣በሚል ፕሮፓጋንዳ ሕዝቡን ለማማለል ይሞክራሉ።ሕዝቡ ግን ይዋል ይደር እንጂ እውነቱ ይገለጽለታል፤እዬተገለጸለትም ነው።

ከዚያም ባለፈ በዬስበቡ ያላቸውን መሳሪያ አንድ ጊዜ በከተማ  አደባባይ፣ሌላ ጊዜ በአዬር ላይ ትዕይንት እያሳዩ ሽብርና ፍርሃት ለመፍጠር ይሞክራሉ።የሕዝብን ጥያቄ ከመመለስ ይልቅ በጥይት እዬገደሉ መኖርን መርጠዋል።ውሃ ላለ ጥይት፣ዳቦ ላለ ጥይት፣ሥራ ላለ ጥይት፣ቤት ላለ ጥይት ለሁሉም ጥይት!

አምባ ገነኖች ሁል ጊዜም በውሸትና በሃይል ይመካሉ።ከሁለት ዓመት በፊት እንዳደረገው ሁሉ አሁንም አሸባሪዎች ከውስጥና ከውጭ ሊገለብጡኝ ያሴራሉ፤ከገቡበት ገብቼ ከሚኖሩበት አገር ይዤ በማምጣት ቅጣታቸውን ያገኛሉ ሲል የፈረደበትን ኢንተርፖል የራሱ የአካባ ፖሊስ አድርጎ የማዬት ጅልነትን አሳይቷል።ጅል አይሙት እንዲያጫውት ይኗል እንዲህ ነው።ከጅልም ጅል ነሆለል! ይህንኑ ጅልነቱን የሚያረጋግጠው እስከ አርብ ሚያዝያ 27 ቀን ማምሻ ድረስ በራያ አካባቢ በሁኔታው ላይ ይዘግብ የነበረውን እውቁን ጋዜጠኛ ጎበዜ ሲሳይን አፍኖ  ወደ ባሕርዳር ከወሰደ በኋላ በኢትዮጵያ አዬርመንገድ ወደ አዲስ አበባ በመውሰድ እጁን በካቴና አስሮ ይኸውላችሁ በጅቡቲ የሽብር ሥራውን ሲሠራ በጅቡቲ መንግሥትና በኢንተርፖል ትብብር ተይዞ ሊመጣ ችሏል በማለት ውሸት መስማት ለማይታከተው ሕዝብ በሚቆጣጠረው የዜና ማሰራጫ ሁሉ ሲቀደድ ውሎ ማምሸቱ ነው።የሚገርመው ነገር ኢንተርፖል አሠራሩን ለውጦ ጥያቄ ሳይቀርብለት ምርመራም ሳያደርግና ሳያጠና ለአብይ አብይ  ሲል የፍጥነት ቢሮ መክፈቱንና ጎበዜ ሲሳይን አሳዶ ይዞ ማስረከቡን አለመግለጡ ነው።እኛም ፍጥነቱን ስናይ ኢንተርፖል ዋና መሥሪያ ቤቱን ጊንጪ ወይም ለቀምት አደረገ እንዴ ብለን ለመጠዬቅ ተገደናል።ሌላው የአነኑ አብይ አህመድ የሚመራው ቡድን ሌላው መሳቂያ ደግሞ በመምህር መስከረም አበራ ላይ ያቀረበው መንግሥትን ለመገልበጥ በቤቷ ውስጥ መድፍና ዲሽቃ መሰብሰቧ ተደርሶባታል ያለው ክስ ነው።ለመሃይም ጎሰኛ  ብዕር ከመድፍና ዲሽቃ አይተናነስም። ያንቀጠቀጣቸው የሰላ ብዕሯ ነው እንጂ በእጇላይ ምላጭ አልተገኘም።ምን ያስገርማል!የባልደራሷን ቀለብ ስዩምንና የአራት ወር ሕጻን ልጇን ጭምር በሽብር ጠርጥሮ ያሰረ ፈሪ ቡድን አይደለምን።

አምባገነኖች መውደቂያቸው ሲቃረብ እንዲህ ያደርጋቸዋል፣ያቅበዘብዛቸዋል፤እብድ ውሻ ይሆናሉ።ሁሉንም ይነክሳሉ፣ስጋት፣ጥርጣሬ ያድርባቸዋል መጨረሻም ላይ በሚፈሩት ሕዝባዊ አመጽ ይወገዳሉ።ይህም ሴረኛ ቡድን መወገዱ ስለማይቀር የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዳለፉት ወንጀለኞች ለፍርድ ሳይቀርቡ እንዳይቀሩ የሚፈለገውን ጥንቃቄና ዝግጅት ማድረግ አለበት።

አሁን ትግሉ ከወሳኝ ደረጃ ላይ ደርሷል፣የአነግ መንግሥት ከወያኔ ጋር ጥምረት ፈጥሮ የጋራ ዓላማቸውን ለማስፈጸም ጦርነት አውጇል፤ሕዝቡም በተለይም አማራው ተነስቶ እዬተፋለመ ነው። የሠራተኛው ማህበር ዓመታዊ በዓሉን ለማክበር ጥያቄ ቢያቀርብ ተከልክሏል፣የኑሮ ውድነት ጠበሰኝ በማለት ብሶትና ምሬቱን ገልጿል፣ነጋዴው በጉልበት ገንዘቡን እዬተቀማ ነው፣የኑሮ ውድነቱ አይጣል ነው፤የገኘው መደብ ግን በየመናፈሻው ውስኪ እዬተራጨ አሸሼ ገዳሜ ይላል።በአልኮል ግፊትም ጦርነት ያውጃል፣በካላላ ኬላ አብይ አህመድም ያወጀው ጦርነት ከተስፋ መቁረጥና ከስካር ጋር የተያያዘ የድምር ውጤት ነው። የአማራው ክልል ተላላኪው የባእዴን ቡድን ጓዙን ጠቅልሎ አራት ኪሎ ከገባ ሰነባብቷል።አዲስ አበባን የጦርነት ጭስ እያጠናት ነው።

በአማራው ክልል የተላከው የአነግ ወራሪ  እንደ ቅጠል እዬረገፈ የወታደር መኪና ጢት የወሰደውን ወታደር ማታ አስከሬኑን ጭኖ መመለስ ግድ ሆኖበታል።በዚህ ጭንቅ ውስጥ የገባው የአነግ መራሹ ወታደር ግማሹም አልዋጋም ብሎ በመኰብለልና ከፋኖ ጋር በመቀላቀል ላይ ነው።የለውጥ ሰደድ ተቀጣጥሏል።ሰደዱ ህወሃትንና አነግን ሳይበላ አይዳፈንም።ትግሉ የሞት የሽረት ሆኗል።የአነጉ መሪ አብይ አህመድ አንድ ጊዜ በሽማግሌ ፣ሌላ ጊዜ በማስፈራራት ተቃውሞውን ለመገደብ መጣሩን ተያይዞታል።ለገበሬው ዘርና ማዳበሪያ፣ለሠራተኛው ደመወዙን የማስገደጃ መሳሪያ አድርጎታል።እኛም ትግል እንኳንስ ደመወዝ፣እንኳንስ ማዳበሪያና ዘር ህይወትንም ይጠይቃልና አታሸብርኑ እንላለን።አገር ሳይኖር ከቶ የትና እንዴት ሆኖ አምርቶና ሠርቶ መብላት ይቻላል? በሽማግሌ ስም የሚመጣውን የቁራ መላከተኛ አደብ እንዲገዛና አርፎ እንዲቀመጥ ማድረግ ተገቢ ነው። የሥርዓቱ አገልጋይ ሆነው ፋኖን በመቃወም፣ሕዝባዊ ትግሉ እንዲኮላሽ ፣ሥርዓቱን እንዲደግፍ ሕዝብ የሚያስገድዱትንም እንዲሁ ተገቢውን እርምጃ በመውሰድ ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ማድረግ ያስፈልጋል።ባለፈው ስርጭታችንም ያልነው ቢኖር ጽዳትና ዘመቻው ከቅርብ መጀመር እንዳለበት ነበር።አሁንም ያንኑ እንደግማለን።

ወያኔና አነግ በደቡብ አፍሪካ የተስማሙትን የራያና የወልቃይት መሬት ከአማራው የመንጠቁ ሂደት ከዳር ላይ ለማድረስ ዙሪያ ከበባ በማድረግ ላይ ናቸው።አማራውን በያቅጣጫው በመከበብ ፋታ የመንሳትና ትጥቅ የማስፈታት ብሎም እስከመጨረሻው እንዳያንሰራራ ለማድረግ ቆርጠው ተነስተዋል።በውጭ ሃይሎችም እዬተረዱ ነው። ምዕራባውያን የግብረሰዶምን እርኩስ ልማድ በኢትዮጵያ ላይ ለማስፈን ከአብይ ጋር ተስማምተው በሰብአዊ መብት ሽፋን በሕግ ሊጸድቅ እንደሆነ ይሰማል፤ለገንዘብ እርዳታቸውም ያስቀመጡት አንዱና ዋናው መስፈርት ይህንኑ ነው።አብይ አህመድ ለገንዘብና ለሥልጣኑ የማይገባው ውል የለም። ቤተእምነቶች ይህንን ሰይጣናዊ ምግባር ሊከላከሉት ይገባል። አማራው በሁሉም ቦታ እምቢ ብሎ እዬተፋለመ ነው።በአገር መከላከያ ስም የአነግ አሸባሪና ወራሪ ሃይልም በከተማዎች ነዋሪ ላይ ተኩስ እዬከፈተ ንጹሃንን በመግደል ላይ ነው።በአዬርና በዬብስ ሃይሉን እያጓጓዘ መግደሉን፣ማቁሰሉን ቤት

ለቤት እዩዞረም መዝረፉን፤መስረቁንና ሴቶችን መድፈሩን ተያይዞታል።በውጭና በውስጥ ያለው አገር ወዳድ ትግሉን መቀላቀል ያለበት ወሳኝ ጊዜ አሁን ነው።

1 ከመንግሥት ጋር ያለውን ማንኛውንም ግንኙነት ማቋረጥ፣ሕዝባዊ እምቢተኝነቱን ከዳር እስከዳር ማቀጣጠል፣የከባቢ አስተዳደሮችን መቆጣጠር፣

በተለይም የአማራው ትግል የባእዴንንና መሰሎቹን የወንጀል ተጋሪዎችን የትግል አጋር የማድረግ አባዜ እንዳያድርበት መጠንቀቅ፣ጽዳቱን ከራሱ ቤት እንዲጀምር ማድረግ፣ትግሉ ባስመሳይ ሃይሎች እንዳይጠለፍ በንቃት መጠበቅ፣ጠላትና ወዳጅን መለዬት፣

2 ለሚዋደቀው አገር ወዳድ ስንቅና ትጥቅ ማቅረብ፣ቤተሰቦቹን መጠበቅና መንከባከብ፣

3 በውስጥና በውጭ ያለው የለውጥ ሃይል የትግል ስልቶችን የሚነድፍና የሚመራ የጋራ አስተባባሪ አካል መፍጠር

በዚህ መልክ የተመራ ትግል ለድል መብቃቱ አያጠራጥርም። በሥልጣን ላይ ያለው አጥፊ ቡድን ለጊዜውም ቢሆን የሚያጠቃው በመደራጀቱና አመራር ስላለው እንጂ ሕዝብ ተከትሎት አይደለም።ያልተደራጀ ሕዝብ በተደራጀ ወንበዴ ለጊዜውም ቢሆን ይሸነፋል። ለዚያም ነው ደግመን ደጋግመን ድርጅት፣ድርጅት፣አሁንም ድርጅት የምንለው።

ያልተደራጀው ይደራጅ!ሕዝባዊ ትግሉን ይቀላቀል!